# ከቤት ማስወጣትን ለመቅረፍ እርምጃ ይውሰዱ

CDC ከቤት የማስወጣት እገዳ

ክፍያ ባለመከፈል ምክኒያት የሚደረግ ከቤት ማስለቀቅን ይከላከሉ

አገልግሎቶች እና ሀብቶች

## CDC ከቤት የማስወጣት እገዳ (ጁላይ 31፣ 2021 ጊዜው የሚያበቃ)

- **የኪራይ ክፍያ ያለመክፈል ከቤት ማስለቀቅን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፉ**
  የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላት (CDC) የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል ትእዛዝ ሰጥቷል። ትዕዛዙ እና የትእዛዙ ዝርዝሮች፣ በፌዴራል ፍ/ቤት ትዕዛዝ እስካልተከለከለ ድረስ ከሰፕቴምበር 4፣ 2020 እስከ ጁላይ 31፣ 2021 ድረስ ኪራይ ባለመከፈል ምክኒያት የሚደረግ ከቤት ማስወጣትን ያግዳል። በሚተገበርበት ቦታ፣ የCDC ኪራይ ባለመከፈል ምክኒያት የሚደረግ ከቤት የማስለቀቅ ጥበቃን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ይችላል ነገር ግን ጥበቃዎች ራስ-ሰር አይደሉም!! ከቤት የማስወጣት ጥበቃን ለማግኘት ብቁ መሆንዎን ለማየት፣ የCDC መግለጫን ይዳሱ እና ከዚህ በታች የሚገኘውን ቪዲዮ ይመልከቱ፡
  - ✓ **የእንግሊዝኛ መግለጫ፡** https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/downloads/EvictionDeclare_d508.pdf
  - ✓ **የተተረጎመ መግለጫ** በአማሪኛ (አማርኛ), በሄይቲያን ክሪኦል (Kreyòl Ayisyen), በሂንዲ (हिंदी), በራሺኛ (Русский), በሶማሊኛ (Soomaali), በስፓኒሽ (Español), በባህላዊ ቻይኒኛ (簡體字) ይገኛል። https://www.hud.gov/program_offices/public_indian_housing/covid_19_resources/rdf_other_languages
  - ✓ **ብቁ መሆንዎን ለመረዳት የሚረዳ ቪዲዮ፡** https://www.youtube.com/watch?v=oODmNuXazqg

  ለCDC ከቤት የማስለቀቅ ጥበቃ ብቁ ከሆኑ፣ መግለጫውን ማንበብ እና መፈረም ከዛም ለ PHA (በሕዝብ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ) ወይም ለአከራዩ (የቫውቸር ተሳታፊ ከሆኑ) መስጠት አለብዎት። ይህንን በፖስታ፣ በኢሜይል፣ በፋክስ ወይም በአካል መፈጸም ይችላሉ። ለመዝገብዎ የመግለጫውን ቅጅ ይያዙ።

- **የCDC ከቤት የማስለቀቅ እገዳ ኪራይን ይቅር አይልም**
  - ✓ በፌዴራል ህጎች ምክንያት፣ PHAዎች ያልተከፈለ ኪራይን ይቅር ማለት አይችሉም።
  - ✓ ለCDC ከቤት የማስለቀቅ እገዳ ብቁ ከሆኑ፣ ኪራይ አሁንም የሚከፈል መሆኑን ያስታውሱ እናም ካልተከፈለ፣ ማንኛቸውም ያልተከፈሉ የኪራይ ክፍያዎች መጠን ይቀጥላሉ።
  - ✓ ከጁን 30፣ 2021 በኋላ ከቤት ማስለቀቅን ለመከላከል ምን ሃብቶች እንዳሉዎት ለማወቅ **ማንበብዎን ይቀጥሉ።**

- **በአሁኑ ጊዜ ለCDC ከቤት የማስለቀቅ ጥበቃ ብቁ ለሆኑት - ከኦገስት 1፣ 2021 ጀምሮ የሚደረጉ ለውጦች፡**
  - ✓ በግዛቱ ወይም በአከባቢው ሕግ መሠረት ረዘም ላለ ጊዜ ከቤት የማስለቀቅ እገዳ እስካልተደነገገ ድረስ፣ የእርስዎ PHA ወይም አከራይዎ የኪራይ ክፍያዎን ካልከፈሉ ወይም በአከራዩ ወይም በPHAው በኩል ድጋሚ የመክፈያ ስምምነት ካለ ድጋሚ የመክፈል ስምምነት ውስጥ ካልገቡ በስተቀር ሊያባርሩዎት ይችላሉ።
  - ✓ **የፌደራል ሕግ የኪራይ ክፍያን ባለመክፈል ለሚደረግ ከቤት ማስለቀቅ የ 30 ቀናት ማስታወቂያን ይጠይቃል**፣ ነገር ግን በግዛት ወይም በአከባቢ ሕግ ረዘም ያለ የማስታወቂያ ጊዜ ሊያስፈልግ ይችላል።

## ኪራይ ባለመከፈል ምክኒያት የሚደረግ ከቤት ማስለቀቅን ይከላከሉ - እነዚህን እርምጃዎች ይውሰዱ

- **_ገቢዎን እንደገና ያረጋግጡ።_** የገቢዎ መቀነስ ወይም የሁኔታዎች ለውጥ ከነበረብዎት፣ PHAን ገቢዎን እንደገና እንዲያረጋግጥልዎት ይጠይቁ።
  - ✓ PHA የወቅቱ ገቢዎን ገምግሞ ለውጡን የሚያንፀባርቅ ሁኔታ ኪራይዎን ያስተካክላል።
  - ✓ ጠቃሚ ምክር! የገቢ ለውጡ በፍጥነት ካልተዘገበ፣ PHAን ስለ ወደኋላ በሚመለሱ የኪራይ ማስተካከያዎች ላይ ያላቸውን ፖሊሲ ይጠይቁ (አንዳንዶች ሊፈቅዱ ይችላሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ላይፈቅዱ ይችላሉ)።
  - ✓ የገቢ ቅነሳ ወይም የሁኔታዎች ለውጥ አጋጥመዎት ከነበረ፣ PHA ገቢዎን እንደገና እንዲያረጋግጥልዎት ይጠይቁ።
- **_የአንድ ጊዜ ድምር ክፍያ_**. ያለፈውን ኪራይ እስከ ጁላይ 31፣ 2021 ባለው ጊዜ በአንድ ጊዜ መክፈል ይችላሉ።
  - ✓ ጠቃሚ ምክር! የማነቃቂያ ክፍያዎች፣ በሳምንት $300 ወይም “ተጨማሪ” የኮቪድ ሥራ እጥነት ክፍያዎች፣ የገቢ ግብር ተመላሽ ገንዘቦች እና የልጆች ግብር ክሬዲት ክፍያዎች በዓመታዊ የገቢ ሂሳብዎ ውስጥ ስላልተካተቱ ያልተከፈለ ኪራይዎን ለማገዝ እንደ ግብአት ያገለግልዎታል።
  - ✓ የማነቃቂያ ክፍያ ካልተቀበሉ፣ የክፍያዎን ሁኔታ ለመፈተሽ እና ቀለል ያለ ቅጽ ለመሙላት እባክዎ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡ https://www.irs.gov/coronavirus/get-my-payment።
- **_ድንገተኛ የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም_ (ERAP)።** ያለፈ የቤት ኪራይ ዕዳ ካለብዎት እና ከቤት የማስለቀቅ አደጋ ላይ ከሆኑ ለአዳዲስ የኪራይ ዕርዳታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ ፕሮግራም መረጃ እዚህ ይገኛል፡ https://home.treasury.gov/policy-issues/cares/emergency-rental-assistance-program። ትግበራ እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች እንደየ ግዛቱ/አካባቢው ሁኔታ ይለያያሉ።
- **አካባቢያዊ ሀብቶች።** ኪራይዎ፣ ፍጆታዎችዎ እና ሌሎች መሰረታዊ ፍላጎቶችዎን ለማገዝ የእርስዎ PHA ስለ ሌሎች ሀብቶች ሊያውቅ ይችላል።
  - ✓ ስለ ድንገተኛ የገንዘብ ድጋፍ መረጃ ለማግኘት 211 ላይ ይደውሉ ወይም 211.orgን ይጎብኙ።
  - ✓ ለእርስዎ የሚገኙትን ሀብቶች ዝርዝር ለማግኘት **_ማንበብዎን ይቀጥሉ።_**
- **_የእንደገና ክፍያ ስምምነት።_** ያለፈ ኪራይዎን ወዲያውኑ መክፈል የማይችሉ ከሆነ፣ ለማንኛውም ያልተከፈለ ኪራይ የእንደገና **_ክፍያ ስምምነት_** ለመግባት የሚችሉ እንደሆነ PHAን ወይም አከራይዎን (የቫውቸር ተሳታፊ ከሆኑ) ይጠይቁ።
  - ✓ ወደ እንደገና ክፍያ ስምምነት መግባት በ PHA ወይም በአከራዩ ውሳኔ የሚሆን ይሆናል።
  - ✓ _የህዝብ መኖሪያ ቤት ተሳታፊዎች፡_ የክፍያ ስምምነት ውሉ በ PHA የመግቢያ እና ቀጣይ የሥራ ፖሊሲ (ACOP) እንዲሁም በጽሑፍ ክፍያ ስምምነት ውስጥ ይገለጻል።
  - ✓ _የቫውቸር ተሳታፊዎች፡_ የእንደገና ክፍያውን ውሎች ለመወሰን በቀጥታ ከአከራይዎ ጋር መደራደር ያስፈልግዎታል።
- **_የተከራይ መብቶች እና በተሳሳተ ሁኔታ ከቤት ማስለቀቅ።_** በስህተት ከቤትዎ እንዲወጡ እየተደረገ እንደሆነ ከተሰማዎት፣ የአከባቢዎን የሕግ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት ኤጄንሲዎችን ያነጋግሩ።
  - ✓ _የሕዝብ መኖሪያ ቤት ተሳታፊዎች፡_ በኪራይ ውልዎ ውስጥ እንደተጠቀሰው አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዎት።
  - ✓ _የቫውቸር ተሳታፊዎች፡_ የአካባቢዎን PHAንም ማነጋገር ይችላሉ።
  - ✓ ጠቃሚ ምክር! **_በአካባቢዎ ስለሚገኘው የሕግ ድጋፍ_** ተጨማሪ መረጃ በሕጋዊ አገልግሎቶች ኮርፖሬሽን (https://www.lsc.gov/what-legal-aid/find-legal-aid)፣ በACL የአዛውንቶች እንክብካቤ መገኛ (https://eldercare.acl.gov/Public/Index.aspx)፣ እንዲሁም LawHelp.org (https://www.lawhelp.org/)ይገኛል።[1]
- **_መድልዎን ሪፖርት ለማድረግ_ HUDን _ያነጋግሩ።_** መድልዎ ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ HUD በስልክ ወይም በመስመር ላይ ቅሬታዎን እንዲያቀርቡ ያበረታታዎታል።
  - ✓ ይደውሉ፡ 1 -800-669-9777
  - ✓ በመስመር ላይ፡ https://www.hud.gov/program_offices/fair_housing_equal_opp/online-complaint

[1] HUD እነዚህን አገናኞች ሚያቀርበው ለእርስዎ ግንዛቤ ብቻ ነው። HUD እነዚህን ድህረ ገጾች አልገመገመም እንዲሁም አይደግፍም።

# ከኮቪድ ጋር የተዛመዱ አገልግሎቶች እና ሀብቶች ለእርስዎ ይገኛሉ

HUD በዚህ ሰነድ ውስጥ በርካታ ሀብቶችን የሚያቀርበው ለግንዛቤዎ ብቻ ነው። HUD እነዚህን ድህረ ገጾች አልገመገመም እንዲሁም አይደግፍም።

- **የHUD የመረጃ ምንጭ ማዕከል (IRC)፡** ስለ HUD ፕሮግራሞች አጠቃላይ መረጃ HUD-PIHRC@ArdentInc.com ላይ ኢሜይል ያድርጉ ወይም 1.800.955.2232 ላይ ይደውሉ።

- **ብሔራዊ የቤት ውስጥ ጥቃት የስልክ መስመር፡** https://www.thehotline.org ወይም 1 (800) 799–7233 ወይም TTY 1 (800) 787-3224 - የቤት ውስጥ ጥቃት ለሚደርስበት፣ መረጃን ለሚፈልግ ወይም የግንኙነታቸው ጤናማ ያልሆኑ ጉዳዮችን ለሚጠይቁ ሁሉ ሚስጥራዊ የስልክ መስመር ነው። በስልክ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መናገር ካልቻሉ LOVEIS ብለው ወደ 1 (866) 331-9474 አጭር መልእክት ይላኩ ወይም የመስመር ላይ ውይይትን ለመጀመር ድር ጣቢያውን ይጎብኙ።

- **211፡** 211 ላይ ይደውሉ ወይም 211.org ን ይጎብኙና በዚፕ ኮድ ያስሱ። ይህ እንደ የቤት ኪራይ እና የፍጆታዎች ድጋፍን የመሳሰሉ ከአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ጋር እንዲሁም ሌሎች በማኅበረሰብዎ ውስጥ ያሉ የድጋፍ አገልግሎቶች ጋር ሊያገናኝዎት የሚችል የስልክ መስመር ነው። ሁሉም ጥሪዎች ሚስጥራዊ ናቸው፣ ስም-አልባ ሊደረጉ ይችላሉ፣ እንዲሁም ደዋዮች በ 180 ቋንቋዎች የትርጉም አገልግሎቶችን መጠየቅ ይችላሉ።

- **የሥራ እጥነት ዋስትና፡** www.usa.gov/unemployment – ለሥራ እጥነት ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ መሆንዎን እና በክልልዎ ውስጥ እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ይወቁ። አዲሱ የፌዴራል ህግ ለግል ሠራተኞች እና ለጊግ ሠራተኞች የሥራ እጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን ይሰጣል፣ **ለሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅሞች ተጨማሪ** $300 ይጨምራል እናም ጥቅማ ጥቅሞች የሚገኙበት የሳምንታት ቁጥርን ያራዝማል። በተጨማሪም፣ ግዛቶች ከኮቪድ-19 ጋር የተዛመዱ አዳዲስ የሥራ እጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን እንዲያቀርቡ ይፈቀድላቸዋል፣ ለምሳሌ አንድ ሰው በተጋላጭነት ወይም በበሽታ የመያዝ አደጋ ምክንያት ወይም የቤተሰቡን አባል ለመንከባከብ ሥራውን ለቅቆ ሲወጣ፤ በኮቪድ-19 ምክንያት አሠሪው ለጊዜው ሥራውን ሲያቆም፤ ይህም ማለት ሠራተኞች ወደ ሥራ መሄድ አይችሉም ማለት ነው፤ ወይም አንድ ሰው ለብቻው እንዲገለል ከተደረገ ነገር ግን የኳራንቲኑ መጠናቀቅ በኋላ ወደ ሥራው የሚመለስ ከሆነ።

- **የኢኮኖሚ ተጽዕኖ ክፍያዎች (አነቃቂ ክፍያዎች)፡** https://www.irs.gov/coronavirus/get-my-payment እስከ $1,400 ለሚደርስ አዲሱ የኢኮኖሚ ተጽዕኖ ክፍያዎች ብቁ መሆንዎን እና እንዴት ክፍያዎን መጠየቅ እንደሚችሉ ይወቁ። ያለፉትን የማነቃቂያ ክፍያዎች ቀድሞውኑ ካልተቀበሉ (የመጀመሪያዎቹ እና ሁለተኛዎቹ ዙሮች በ 2020 እና በጃንዋሪ 2021 ነበር የተሰጡት)፣ ይህ ድህረ-ገጽ ብቁነትዎን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚችሉ እና እነዚያን ክፍያዎች እንዴት መጠየቅ እንደሚችሉም መረጃ ይዟል።

- **ነፃ የግብር ዝግጅት እና አዲስ የሕፃናት ግብር ክሬዲት፡** https://www.irs.gov/individuals/free-tax-return-preparation-for-qualifying-taxpayers – በሠለጠኑ በጎ ፈቃደኞች የቀረበን፣ ነጻ ግብርን የመሙላይ እገዛን ያግኙ ወይም በመስመር ላይ በነጻ e-file ያድርጉ። በተለምዶ ግብርን ተመላሽ የማያደርጉና ልጆች ያሎት ከሆነ፣ ለአዲሱ የህፃናት ግብር ክሬዲት ብቁ ለመሆን በዚህ ዓመት ለማስገባት ማሰብ አለብዎት። አዲሱ የፌዴራል ሕግ ዕድሜያቸው ከ 6 ዓመት በላይ ለሆኑ እያንዳንዱ ሕፃናት እስከ $3000 ድረስ እንዲሁም እድሚያቸው ከ 6 አመት በታች ለሆኑ ማናቸውም ልጆች እስከ $3600 የልጆች ግብር ክሬዲቶችን ከፍ አድርጓል። **ወርሃዊ ክፍያዎች እስከ ክረምት መጀመሪያ ሊላኩ ይችላሉ፣ ነገር ግን ቤተሰቦች ገንዘቡን ለመቀበል ተመላሽ ግብርን ማሳወቅ አለባቸው።** ለ 2020 ለማመልከት ቀነ-ገደቡ ሜይ 17፣ 2021 ነው

- **የአደጋ ጭንቀት የእርዳታ መስመር፡** 1 (800) 985-5990 (ይደውሉ ወይም መልእክት ይጻፉ) - ኮቪድ-19ን ጨምሮ ከማንኛውም አደጋ ጋር የተዛመደ የስሜት መቃወስ እየተሰማቸው ላሉ ሰዎች ፈጣን የችግር ግዜ ማማከር ለመስጠት የተመሰረተ ብሔራዊ የስልክ መስመር ነው።

- **የማህበረሰብ ድርጊት ኤጀንሲ፡** https://communityactionpartnership.com/find-a-cap/ – በአካባቢዎ ያለ የማህበረሰብ ድርጊት ኤጀንሲን የቤት ኪራይ ወይም ፍጆታዎች ድንገተኛ የክፍያ ድጋፍ የመሳሰሉ ምን ዓይነት አገልግሎቶችን እንደሚሰጡ ለማወቅ ያነጋግሩቸው።

- **የክፍያዎች እገዛ፡** www.usa.gov/help-with-bills ለስልክ አገልግሎት፣ ለሃይል ክፍያዎች እና ለሌሎች ወጭዎች ክፍያ እርዳታ፤ ስለመንግስት ፕሮግራሞች ይወቁ።

- **የጥቅማ ጥቅም ብቁነት፡** www.benefits.gov - ለምን አይነት የመንግስት ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ እንደሆኑ ይወቁ፣ ለምሳሌ እንደ ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጋፍ (TANF)፣ የምግብ ዕርዳታ እና የጤና አጠባበቅ የመሳሰሉ።

- **የኮቪድ-19 ክትባት መረጃ፡** https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/vaccines/ – ስለ ኮቪድ-19 ክትባት ምን ያህል፣ ውጤታማ እንደሆነ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እና እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይወቁ።

- **የትምህርት ግብዓቶች፡** https://bealearninghero.org/parentstrong-2/ – ልጆቻቸው በቤት ውስጥ እንዲማሩ ለሚረዱ ወላጆች ወይም ለልጆቻቸው ተጨማሪ የትምህርት ግብዓቶችን ለማግኘት ለሚፈልጉ ወላጆች የትምህርት መረጃዎችን እና ድጋፍ ያግኙ።